## መንዜው አጉኔ አለቃችንና ተስፋዬ ገ/ አብ

- በተስፋዬ ገ/አብ የስደተኛው ጋዜጠኛ መጽሃፍ ላይ ሰሞኑን ዲያስፖራው ቁርቋሶ ከመጀመሩ በፊት ፤ላይፍ ለተባለ መጽሄት ተስፋዬ ገ/አብ ቃለ መጠየቅ ሰጥቶ ነበር ። ኢህአፓ እንደኮለኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም መጽሃፍ አሻጥር ቢያደርግብህ በምን ትቋቋመዋለህ ተብሎ ሲጠየቅ ? አበጥ አበጥ ያሉ ገታሪ ጠበቆች ፣ አሳታሚውም ድርጅት ሆነ እኔ ስላሉን በሱ አታስቡ ነበር ያለው ። ቀስ ብሎ ግን ከወደ አመስተርዳም አንድ ዳጎስ ያለ ዶሴ ፣ በዳኛ ወልደሚካኤል በኩል ብቅ አለ ። ዲያስፖራው ተንጫጫ ። ድሮስ ! ተናግረን አልነበረ? ይህ ደራሲ እንደ ወገምት ይዞናል ! መች ይለቀንና ! እሱ ምን ያድርግ ! ከውስጣችን የወሸቁት የኛ ሰዎች.... ብዙ አይነት ንዴት ፥እልህ ፥ቁጭት ወዘተ ጨሰ ። በዚያም ሰፈር በኩል ፣ እነ አይጋ ፥ ትግራይ ኦን ላይን አጫጫሱት ። አብሪ ባትሪም ወደ ሰማይ አጎኑ ።

- በውጭ አገር ያሉ ፣ በዛ ያሉ ነጻ ድረ ገጾች ነን የሚሉ ሁሉ በዳኛ ወልደሚካኤል አጋላጭ ጽሁፍ ላይም ሆነ ፣ በአሌክስ_ሊክስ የአራዳ ዘበኛ ሚስጢር ጎልጓይነት ሥራ ባለመስማማት ይሁን ወይ ኤዲቶሪያል ቦርዳቸው ባለመፍቀዱ ምክንያት ዳጎስ ያለውን ጽሁፍ አገዱት ። ፌስ ቡኮች ነገሩን አቀጣጠሉት። አካበዱትም። አጥቅተውም ታትሞ ሊሸቀል በዝግጅት ላይ የነበረው መጽሃፍ መከነ ። በመጨረሻም በራሱ በጸሃፊው በፒዲኤፍ በነጻ ተበተነ።

- ብዙ ፓልቶኮች ሳይሆኑ ፣ አንድ የፓልቶክ ክፍል ብቻ ጉዳዩን አጮኸው ። ከማጮኹም አልፎ ፤የተቃውሞ ደቦ በማስተባበር የተስፋዬ ገ/ አብን መጽሃፍ አሳታሚው ድርጅት ከህትመት ውጭ እንዲያስወጣው የፊርማ ደቦ አፋፋመበት ። ደቦው የሠራ መስሏል ። ትንሽ ቆይቶ ከመጽሃፉ ምዕራፍ ሰባትን ካላወጣህ አናትምልህም የተባለው ተስፋዬ ፣ ጽሁፌን አልቀነጥስም ፣ ባታትሙት ተዉት እንጂ ብሎ ፣ በነጻ በተነው ።
- ነጻነት አሳታሚ ድርጅት የተባለው ድርጅት ፣ ለጊዜው እፎይታ ያገኘ ይመስላል ። ውሉን ቢያፈርስም ፣ አሳታሚው ድርጅት ግን አሁንም የአሰፋ አባተን የቀድሞ ዘፈን ከማዜም አላቆመም ይሉታል ተቺዎቹ ።

ፊርማና ወረቀት ቀሪ ነው ተቀዳጅ፣
መተማመን ብቻ ይበቃል ለወዳጅ ።

የፌስ ቡክ ነገር ቢነሳ አንድ በአረቡ ዓለም ሰሞኑን የሚቀለደውን ቀልድ ላልሰማችሁ ፣ እንድትሰሙት ፈለግሁ ። እንዲህ ነው ቀልዱ ። ሆስኒ ሙባረክ ሞተና ሰማይ ቤት ሲደርስ ከበር ላይ ጀማል አብዱል ናስር፥ አንዋር ሳዳት ሆነው ፣ ለሙባረክ ሞቅ ያለ አቀባበል ያደርጉለታል ። በምን ምክንያት እንደ ሞተ ተራ በተራ ይጠይቁታል ። የመጀመርያውን ጥያቄ ጀማል አብዱልናስር ይጠይቃል... አንተንም እንደኔ በመድሃኒት መርዘው ነው የገደሉህ ? ኧረ በጭራሻ ይላል። ሳዳት ይቀጥላል ፣ እንደኔ በጥይት ነው የገደሉህ ይላል ? ሙባረክ አሁንም ኧረ በጭራሽ ! ሁለቱም በመጨረሻ በመገረም  ታድያ በምንድነው የገደሉህ ቢሉት ? በፌስ ቡክ! ጀማል አብዱልናስርም ሆነ ሳዳት ፌስ ቡክን አያውቁትም ።

የዛሬ ሶስት ዓመት ግድም ፣ በአመስተርዳም ከተማ በተዘጋጀው የአውሮፓ ኢትዮጵያውያን የስፖርት ፌስቲቫል ላይ የዚህ ጽሁፍ ጸሃፊ ጋዜጠኛና ደራሲን ተስፋዬ ገ/ አብን እዚያው ስታዲዮሙ ቅጥር ግቢው ውስጥ ባለ መዝናኛ ክበብ ውስጥ ቢራ ሲጎነጭ አግኝቼው ለመቀላቀል ብዬ በትሪ ቢራ ይዤ ቁጭ አልኩ ። ተስፋዬ ጀርባውን ወደ በሩ ሰጥቶ ያለምንም ፍርሃት ቢራውን ይጎነጫል ። ሁለታችንንም የሚያውቅ አንድ ታላቅ ደራሲ አስተዋወቀንና ጨዋታ ጀመርን ። ወያኔን የመሰለ ታላቅ ጠላት አለኝ እያልክ እንዴት ጀርባህን ሰጥተህ ትዝናናለህ ? ነበር የኔ የመጀመርያ ጥያቄ ? ተስፋዬ ወደ ሰማይ እያሳየኝ ... ከገላገሉኝማ እሰየው አለኝ ። አልገባኝም ። ለምን ? የሚል ነገር በውስጤ ተጫረ ። ጨዋታው ደራ!  በቡርቃ ዝምታ ላይ የነበረኝን ብስጭት ገለጽኩለት ። አይናደድም እሱ ! ጭራሽ ሰው ያበግናል እንጂ ። ወደ ታሪክ ገባን ። ዘራይ ደረስን አነሳን ። አሁን ጨዋታው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ ወደ ሚባል ደረጃ ተዳረስን ። ዘራይ ደረሰ ለኢትዮጵያ ባንዲራ ሲል ጎራዴውን ከአፎቱ ስቦ ጣልያን አገር ሰው ጨረሰ የምትሉት ባዶ ተረት ነው ። ለኢትዮጵያ ባንዲራም ሳንጃውን አልሳበም ፣ ለወደፊቱ በዚህ ላይ እጽፋለሁ አለኝ ። እኔም ጻፍ ! ኢትዮጵያ የታሪክ ጸሃፊ መካን አይደለችም ። የዚያን ጊዜ መልስ ታገኛለህ ብዬ በመከባበር ተለያየን ።

በአንድ ገዥ መደብ ላይ ቂም የያዙ ሰዎች ፣ ጥርስ ሲነክሱ ፣ ገዢዎቹ መደቦች ላይ ብቻ ሳይሆን አገራትም ላይ ጥርስ ይነክሳሉ ። ለዚህ ደግሞ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ጋዜጠኛ አይናር ሉንድ የተባለው ኖርዌጅያዊ ጋዜጠኛ ልክ እንደ ተስፋዬ ገ/አብ በኢትዮጵያ ላይ አቂሞ የጻፈው Paradisveien/ የገነት ጎዳና የተባለው እንደ አብነት የሚጠቀስ መጽሃፍ ነው ። ይህ ጋዜጠኛ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ 1973/75 በኢትዮጵያ ብስራተ ወንጌል ተብሎ በሚጠራው ድርጅት ውስጥ በሚሰራበት ወቅት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የተገለበጠበት ወቅት በመሆኑ ፣ ከደርጎች ጋር ጸብ ውስጥ ይገባል ። የጸጥታ ሠራተኞች ዘወትር መውጫና መግቢያውን እየተከታተሉ መግቢያ መውጫ ያሳጡታል ። ያስሩታልም ።

አይናር ሉንድ እኤአ. በ-1995 ለኖርዌጅያን አረጋውያን የእንቅልፍ ማስተኛ የጻፈውን ኢትዮጵያውያንን የተመለከተ የተረት መጽሃፉን እንዲህ ይተርክልናል ። በቮክስዋገን የፖሊስ መኪና ከሚከታተሉኝ ፖሊሶች ትንሽ ለመገላገል ብዬ ፣ ስዊድኖች ካሰሩት ህንጻ ኮሌጅ ባሻገር ካለው ሸዋ ዳቦ ተብሎ ከሚጠራው ዳቦ ቤት ተኮልኩለው ሰልፍ ከያዙት ሰዎች ኋላ ሄጄ ተሰለፍኩ ።ሁል ጊዜ ዳቦ የምገዛው ከዛ ሸዋ ዳቦ ቤት ስለነበረ ፣ ከዚያ ስሠለፍ አንድ ነገር ትውስ ይለኛል ። ኢትዮጵውያኖች አንድ አፈ ታሪክ አላቸው የሚመጻደቁበት ። እንዲህ ይላሉ ። ፈጣሪ የሰው ልጅን በራሱ አምሳያ ሊፈጥር አሰበና ፣ ሊጥ አቡክቶ ወደ መጋገርያው ምድጃ ውስጥ አስገባው ። በመሃሉ ፈጣርያችን ከሚሯሯጡ ጦጣዎች ጋር ሲላፋና ሲቃለድ የዳቦውን የማውጫ ሰአት ስለዘነጋው ፣ ምድጃውን ሲከፍተው ዳቦው አርሮ ድብን ብሎ ጠቁሮ አገኘው ። ይህን ጊዜ ፈጣሪያችን **ኔግሮ** ብሎ ጠራው ።

በሚቀጥለው ጊዜ ፣ ፈጣርያችን ያቦካውን ሊጥ ምድጃ ውስጥ ከቶ ፣ሰአቱን እንዳይረሳው እጅግ በመፍራት ቸኩሎ ምድጃውን ከፍቶ ዳቦውን አወጣው ። ያለ ሰዓቱ የወጣው ዳቦ እጅግ ነጭ በመሆኑ ፣ ዳቦውን **አውሮፓውያኖች** ብሎ ጠራው ።

በሶስተኛው ጊዜ ደግሞ ፣ ፈጣሪያችን ! እጅግ በመጠንቀቅ ፣ሰአቱን ጠብቆ ፣ ዳቦውን ከምድጃ ሲያወጣው ፣ ያማረና ጠይም ዳቦ በማውጣቱ  ፈጣርያችን እጅግ ተደስቶ ! ፈጣርያችን ይህን ዳቦ **ኢትዮጵያዊ** ብሎ ጠራው ብለው ራሳቸውን ያሞካሻሉ ። በአባባላቸው እኔም እስማማለሁ ይለናል የለበጣ ። ግን ይለናል ራሳቸውን ጠይምና ቆንጆ ያደረጉት ኢትዮጵያውያኖች ገዝተው መብላት የሚወዱት ዳቦ ነጭ መሆኑ ነው ደግሞ የሚገርመኝ ይላል ። አዲስ አበባ ተወልጄ ሳድግ ይህን ተረት በኔ በኩል ሲባል ሰምቼም አላውቅም ።

ጽሁፉን ላለማንዛዛት በማሰብ ነው እንጂ፣ አይናር ሉንድ ፣ ከተስፋዬ ጋር እየተቀባበለ የጻፈውን የሚመስል አይነት አፈ ታሪክ ብዙ በመምዘዝ ከመጽሃፉ ውስጥ ማውጣት ይቻላል ። ልክ እንደ ተስፋዬ ምኒሊክ ግዛታቸውን ሲያስፉፉ የአራት ኪሎውን ቤተ መንግስታቸውን ሲቆረቁሩ ፣የአካባቢውን ህዝብ በመውረር ፥ ወይም ቅኝ በመግዛት ፣ ኢምፓየራቸውን መሰረቱ ይለንና ፣ ኢትዮጵያ ራሷ በአፍሪካ ብቸኛዋ ቅኝ ገዥ ፣ ከምዕራብውያን ጋር በ 1885 ቁጭ ብላ የአፍሪካን ካርታ ያሰመርች አገር ናት ብሎ አይናር ሉንድ ይወርድባታል ።

አይናር ማሚቴ የተባለችውን የቤት ሠራተኛውን አንድ ቀን መጸዳጃ ቤቱን ስታጸዳ ደርሶ ሲመለከት ፣ የመጸዳጃ መቀመጫ ገንዳውን በአይናር የጥርስ ቡሩሽ ስታጥብበት አይቼ በማለት ፣ ኢትዮጵያኖች ከስልጣኔ ምን ያህል ኋላ እንደቀሩ ለአገሩ አረጋውያን ከጻፈው የተረት መጽሃፉ ላይ ማንበብ ይቻላል ። ለምን አይናር ሉንድ እንዲህ በኢትዮጵያውያን ላይ ተዛበተ ? ደርግ አስሮ ጭራሽም ሊረሽነው እንደነበረ ሁሉ መጽሃፉ ላይ ጽፏል ። ከዚያ እልህ በመነሳት ኢትዮጵያ ላይ ጥርስ ነክሷል ። ሰሞነኛ በሆነው ፣ የተስፋዬ መጽሃፍ ላይ አልሄድበትም ። ብዙ ጸሃፍት ሄደውበታል ። በተለይ ቤልጅግ አሊ በጥሩ ሁኔታ ዋና ዋና ነጥቦችን ነቅሶ አሳይቶናል ። ግን ለምን ተስፋዬ ? እንዲህ ያቺን ምድር ጥርስ ነከሰባት ? ከአዲስ አበባ ርቀት በአርባ ኪሎሜትር ላይ ገሳ ለብሶ ፣ የበግ ደበሎ ለብሶ የሚኖረውን ድሃ አማራ ፣ ከድሃ ወገኑ ኦሮሞ ጋር ለምን ሊያጫርሰው ተነሳ ? በማንጓጠጥ ክስ ከተከሰስን ደግሞ የአዲስ አበባ ልጆች እንከሰስ እንጂ ደሃው አማራ በምን እዳው ? አዲስ አበባ ተወልደን ያደገን አማራ ፥ኦሮሞ፥ትግራዋይ፥ ኤርትራዊ፥ ጉራጌ ወዘተ በሙሉ ከገጠር ለመጡት ሰዎች በሙሉ የቅጽል ስም እያወጣን ፣ በአነጋገር ዘዬአቸው እየቀለድን እንደምናንጓጥጣቸው እሙን ነው ። ለምን አማራው ላይ ብቻ ይህ ወቀሳ በተስፋዬ ተቆንጽሎ ይወጣል ? መንዜ ራቱ በጊዜ ፣ ምሳው አስር ጊዜ እያልን አዲስ አበባ ላይ በመንዜው እንቀልዳለን ። በክልሱ ላይ ክልስ አህያ መልስ..... ጸያፍ ነው መዝጊያውን **አልቅስ** እንላለን ። ተስፋዬ ለምን አማራው ነው እንዲህ የሚል እያለ ያጫርሰናል ?

እድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ አንደኛ ክፍል እንደገባሁ ፣ አንድ በዚያን ወቅት እድሜው በግምት 14 የሚሞላው ሞፈሩን ሰቅሎ ከመንዝ የመጣ አንድ **አጉኔ** የሚባል ተማሪ ክፍላችን ውስጥ ይመደባል ። ወቅቱ መስከረም ወር ውስጥ ነውና ሁላችንም ስማችንን እየተነሳን እንድንናገር አስተማሪያችን ያዙናል ። ከመንዝ የመጣው አጉኔ የተባለው ተማሪ ስሙን ሲያስተዋውቅ ስሜ አጉኔ ነው ሲል ክፍሉ ሁሉ በሳቅ ይሞታል ። አጉኔ ተበሳጨ ። የክፍል አለቃ ሆኖ ሲሾም ፣ የሳቅንበትን በሙሉ አፈር እያስገባ ይቀጠቅጠን ነበር ። በኋላ አጉኔ ተምሮ ሲጨርስ የህዝብ ደህንነት ሰራተኛ ሆኖ አይቸዋለሁ ። እነጫልቱ ብቻ ሳይሆኑ ፣እነአጉኔም ፥እነ ባጫ ብቻ ሳይሆኑ እነአብሬም አዲስ አበባ ላይ በስማቸው ይሳቅባቸዋል ። ክሱ ከመጣ የአዲስ አበባ ልጆች ላይ ይሁን እንጂ ለምን አማራው ላይ ተስፍዬ ጎራዴውን ከአፎቱ ይስባል ?

ሰለጠኑ በሚባሉት አገሮች አንዷ ኖርዌይ ውስጥ እስከ አሁን ድረስ የሰሜኖቹን ኖርዌጅያኖች እንዳልሰለጠኑ ፣ በቋንቋ ዘይቤአቸው ጭምር አሁን ድረስ ይቀለድባቸዋል ። እንደውም እኛ መጤዎቹ አገራቸው ከገባን ጀምሮ ነው የሰሜኖቹ ኖርዌጅያኖች ትንሽ አረፍ ያሉትና ፣ አስሎም ሲመጡ ቤት እንዲከራዩ የተፈቀደላቸው ። ማንም የመሃል አገር ኖርዌጅያዊ ለሰሜነኞቹ ኖርዌጅያኖች ቤት አያከራያቸውም ነበር ። በአራዳ ቋንቋ /Load-ሎዱን እኛ ነን ከሰሜኖቹ የወሰድንላቸው ። እኛ ላይ ሲያተኩሩ እነርሱን ትንሽ ረሷቸው ። አሁንም ግን በሥራ ቦታ ሲቀለድባቸውና ገፋ ሲያረጓቸው ይታያል ። ትምህርት የሰውን ልጅ አስተሳሰብ ይለውጣል ። ማንጓጠጥ በሁሉም አለም ላይ አለ ። ትክክል ነው እያልኩ አይደለም ። በትምህርት ይቀየራል ። ግን እንዲህ ትባሉ ነበር ብሎ የጥላቻ መርዝ መቆፈር ፣ የተስፋዬን ህሊና በሰላም የሚያሳድረው ከሆነ ፣ የአይምሮ ጠበብቶች ብቻ ናቸው ችግሩን የሚያውቁለት ። አንድ ፍራቻ ግን አለኝ ። እንደ ሰው ማንም ሰው ሆነ የድርጅት ዓባል ወይም ድርጅት የተስፋዬ የግል ጓደኛ መሆን ይችላል ። በሃገር እና ህዝብ ላይ ግን ከተመጣ ከዚህ ሰው ጋር የሚደርግ ንክኪ ብዙ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል ፣ አካሄዳችንን ቆም ብለን ማየት ይገባናል ። ወያኔን ለማዳከም የገነባናቸው ተቋማት በሙሉ ፣ በአንድ ሰው ምክንያት እንዲፈርሱ መንገድ መክፈት የለብንም ። አብሮነትም ሆነ ወዳጅነት ከግለሰቦች ጋር ይቀጥሉ ። ከተቋማት ጋር ግን ይራራቁ ።

እንግዳ ታደሰ/ ኖርዌይ